የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
የቃል አቀባዩ ቢሮ
ከኤሪሲ አዳም፣ ምክትል ቃል አቀባይ የተሰጠ መግለጫ
ጥቅምት 28 ቀን 1998 ዓ.ም.

የፖለቲካ ነውጥ በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ ያለው ፖለቲካዊ ነውጥ አሜሪካን ያሳዝናታል፡፡ በመሆኑም፣ ሁሉም ወገኖች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለሰመፅ ከሚያነሳሱ፣ በሰው ላይ ጉዳት፣ በሕዝብ ወይም በግል ንብረት ላይ ጥፋት ሊያስከትሉ ከሚችሉ አድራጉቶች ሁሉ እንዲቆጠቡና እንዲከላከሉ ትጠይቃለች፡፡

የአሜሪካና የአውሮፓ ኅብረት አምባሳደሮች በወቅቱ ያለውን ሁኔታ ሊያረጋብ የሚችልና የፖለቲካ ተቀናቃኙ ወገን በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሕይወት ገንቢ ሚና እንዲኖረው የሚያስችል መግለጫ ጥቅምት 27 ቀን በአዲስ አበባ አውጥተዋል፡፡ በዚያ መግለጫ ውስጥ በተጠቀሱት ላይ የኢትዮጵያ መንግሥት እርምጃ እንዲወስድ አሜሪካ ትጠይቃለች፡፡

በተለይም ሕይወት በሚያጠፋ መሣሪያ መጠቀም፣ በዘፈቀደ ፍተሻ፣ ድምሳ ድብደባና በቁጥጥር ሥር ማዋል እንዲያከትሙ፣ የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ፣ እስከዚያም ድረስ ቤተሰቦቻቸው፣ የሕግ አማካሪዎቻቸው እና የቀይ መስቀል ዓለምአቀፋዊ ኮሚቴ ወይም ሌላ የዓለም ኅብረተሰብ ተወካይ ሳይዘገይ አሁኑኑ እንዲጐበኙዋቸው እንዲፈቀድ፣ የመገናኛ ብዙሃን መሪዎች እንዲፈቱ ማስፈለጉን በተለይ እናስምርበታለን፡፡ እንደዚሁም ተቀናቃኙ ወገን ድምጹን በአግባቡ ማሰማት መቻሉን ለማረጋገጥ የፓርላማ የሥራ አመራርና ደንብ ተገምግመው እንዲሻሻሉ፣ ሰኔ 2 ቀን 1997 ዓ.ም. አሁን በቅርቡም በሰው ላይ ሞትና የአካል ጉዳት ያደረሱትን ሁኔታዎች የሚመረምር ነፃ ኮሚሽን እንዲቋቋም፣ እና የግል ዜና ማሰራጫዎች (ጋዜጦች) ሥራቸውን እንዲቀጥሉ መፍቀድና የተመዛዘነና ኃላፊነት የሰፈነበት መረጃ መሰራጨቱን ለማረጋገጥ በሁሉም ወገኖች የሚዘጋጅ የሙያ ሥነ ምግባር መቀረፅ እጅጉን አስፈላጊ ናቸው፡፡